በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 202114

ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካቾች**- 1. ሀድሌ ኢብራሂን

2. ኡመር ኢብራሂን

3. መሀሙድ አደን

4. ኡመር መታን

5. መሀመድ አህመድ አብዲ

6. መታን መሀሙድ

7. መሀመድ አረብ

**ተጠሪዎች**- 1. ጠይብ አብዲላሂ

2. አህመድ ጣሂር አብዲላሂ ሽዴ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ እርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋፈን ዞን ጅግጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካቾች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በሰሀሊቲ ቀበሌ ኮጃርታ ሼህ ጣሂር ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ በሰሜን ሀጂ መሀመድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እና የጎሳ ቦታ፣ በምዕራብ ሙሳ አውሌ፣ በደቡብ ተጠሪዎች፣ በምስራቅ የአመልካቾች መሬት የሚያዋስኑትን ስፋቱ 4 ጋሻ፣ ርዝመቱ ደግሞ 7.5 ጋሻ ጠቅላላ መጠኑ 30 ጋሻ የሆነ የእርሻ መሬት ያለአግባብ ይዘውብናል፤ እንዲለቁልን ብንጠይቃቸው ፍቃደኛ ስላልሆኑ ለቀው እንዲያስረክቡን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀው ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ የያዝነው የአመልካቾች መሬት የለም፤ አመልካቾች ከክሳቸው ጋር ያቀረቡት የባለቤትነት ማስረጃ የለም፤ ክስ የቀረበበትን መሬት ከአባታችን በውርስ ያገኘነው የተጠሪዎች ይዞታ ነው፤ ከበፊት ጀምሮ ስናርሰው የነበርነውም እኛ ነን፤ በዚህ ጊዜ ውስጥም አመልካቾች መሬቱ ይገባናል የሚል ጥያቄ አላቀረቡም፤ አመልካቾች መሬቱን እንዴት እና መቼ እንዳገኙት፤ መቼስ ከይዞታቸው እንደወጣ አልገለጹም፤ አመልካቾች ወደ አካባቢው የገቡት መሬት ገዝተው ሲሆን የገዙትን መሬት የነካባቸው ሰው የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ካደመጠና ከመረመረ በኋላ የአመልካቾችን ክስ ውድቅ በማድረግ ተጠሪዎች መሬቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በወረዳ ፍርድ ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች አሁንም በውሳኔው ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካቾች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች በቀን 01/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ አከራካሪው መሬት የገጠር እርሻ መሬትን የሚመለከት ሲሆን የሚገዛውም በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 128/05 ነው፤ በአዋጁ መሠረት ደግሞ ጉዳዩ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ከመሄዱ አስቀድሞ በአካባቢው በሚገኝ ገበሬ ማህበር ጽ/ቤት፣ ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣ በአካባቢ ሽማግሌዎች እና በጎሳ መሪዎች መታየት እንዳለበት ቢደነግግም የስር ፍርድ ቤቶች የአዋጁን መኖር ዘንግተው ጉዳዩ በዚህ መንገድ እንዲያልፍ አለማድረጋቸው ወይም ትዕዛዝ አለመስጠታቸው፤ ክሱን ያቀረብነውና ዳኝነት የጠየቅነው አመልካቾች ሆነን እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ባልተጠየቀ ዳኝነት ላይ መሬቱ የተጠሪዎች ነው በማለት መወሰናቸው፤ እንዲሁም አመልካቾች ክስ ያቀረብንበት መሬት ስፋት 4 ጋሻ በ7.5 ጋሻ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ግን ከተጠየቀው ዳኝነት በመውጣት ስፋቱ 16 ጋሻ በ5 ጋሻ የሆነ መሬት ላይ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል ከመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ጥሪ የተደረገላቸዉ ቢሆንም ባለመቅረባቸዉ በሌሉበት ክርክሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር

እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የእራሳቸዉ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከአባታቸዉ አብዱላሂ ሺዴ የወረሱት የእራሳቸዉ እንጂ የአመልካቾች አለመሆኑን ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኝ ክርክር ይህ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1) መሠረት መያዝ የሚገባዉ ትክክለኛ ጭብጥ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የአመልካቾች ነዉ ወይስ ተጠሪዎች ከአባታቸዉ በዉርስ ያገኙት ነዉ? የሚል ነዉ፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የወረዳዉ ፍርድ ቤትም በዚሁ መሠረት የግራ ቀኝ ምስክሮችን በመስማት እንዲሁም መሬቱ ከሚገኝበት ቦታ በአካል በመሄድ አጣርቶ ይህንኑ ከግራ ቀኝ ምስክሮች ቃል አንፃር በመመርመር እና በመመዘን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በተጠሪዎች እጅ ያለ እና አመልካቾች መሬቱን ይዘዉት እንደማያዉቁ እና በመሬቱም ላይ መብት እንደሌላቸዉ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ስህተት ካለ እንደመሠረታዊ የህግ ስህተት ታይቶ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል ቢሆንም በተያዘዉ ጉዳይ ከማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የተፈጸመ ግድፈት ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ አያሳይም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ መሬት ላይ መብት የላቸዉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ መሬት ላይ መብት እንዳላቸዉ እና በተጠሪዎች በህገ ወጥ መንገድ የተያዘባቸዉ ስለመሆኑ አመልካቾች በክሳቸዉ መሠረት የማስረዳት ሸክም ያለባቸዉ ሲሆን ይህን ግዴታቸዉን አልተወጡም፤ በአንፃሩ መሬቱ ከተጠሪዎች እጅ ወጥቶ በእጃቸዉ (በአመልካቾች) ገብቶ እንደማያዉቅ የተጠሪዎች ምስክሮች ያስረዱ ቢሆንም ይህ መሆኑ የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ የማድረግ ዉጤት ከሚያስከትል በስተቀር ፍርድ ቤቱ መሬቱ የተጠሪዎች ነዉ በሚል እንዲወስን ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ከመሬቱ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ እና በተጠሪዎች ያላግባብ የተያዘ ስለመሆኑ በክሳቸዉ መሠረት ማስረዳት ካልቻሉ እና/ወይም ይህ ክርክራቸዉ በተጠሪዎች ምስክሮች መስተባበሉን ከተረዱ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ መቆም ሲገባቸዉ ከዚህ በላይ በመሄድ መሬቱ የተጠሪዎች እንዲሆን "ወስኘላቸዋለሁ" በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሥነ ሥርዓት ግድፈት፣ በተለይም የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በተጠየቀዉ ዳኝነት ላይ የተገደበ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 182 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ የሚቃረን፣ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

## ዉሳኔ

1. የጅጅጋ ደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 1411/2011 በቀን 10/10/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 052-34/11/12 በቀን 12/05/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05-1-201/12 በቀን 02/03/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካቾች ከመሬቱ መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት የዳኝነት ጥያቂያቸዉን ዉድቅ በማድረግ የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፤ መሬቱ የተጠሪዎች ነዉ በሚል የተሰጠ ዳኝነት ተሽሯል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም